# የአንደኛ ዓመት
# የስራ ክንዉን ሪፖርት

በኢፌዲሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ

**FDRE Attorney General**
**Legal and Justice Affairs Advisory Council**


**Contact**
Abadir M. Ibrahim, J.S.D.
Phone: +251 (0) 991 73 03 12
E-mail: abadir.m.ibrahim@gmail.com
Organization website: http://ljaac.fag.gov.et

# ማዉጫ

1. መግቢያ 3

1.1 የለውጥ ሂደቱ ዳራ 3
1.2 ዓላማ 4

2. የትግበራ አደረጃጀትና የሰዉ ሀይል 4

3. የ1ኛ ዓመት የስራ ዝርዝርና መርሀ-ግብር 5

3.1 የፍትሕ ጉዳዮች የስራ ቡድን 6
3.2 የሲቪል ማህበረሰብ የስራ ቡድን 6
3.3 የፀረ-ሽብር አዋጅ ማሻሻያ የስራ ቡድን 7
3.4 የሚድያ ህግ የስራ ቡድን 9
3.5 የዴሞክራሲ ተቋማት የስራ ቡድን 10
3.6 የሕግ አወጣጥ ሂደትና የአስተዳደር ሕግ የስራ ቡድን 11
3.7 የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት የስራ ቡድን 12
3.8 የንግድና የፍትሐብሔር ሕግ የስራ ቡድን 13
3.9 የህሕግና ተያያዥ ጉዳዮች አገልግሎት የስራ ቡድን 14

4. ተግዳሮቶች እና የቀጣይ ጊዜ ተስፋዎች 15

4.1. የሰው ሀብት 16
4.2. ቢሮና መሳሪያዎች 16
4.3. በማሻሻያ ሂደቱ የሚደረግ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ 16
4.4. ማህበረሰብ አቀፍ ንቃት ማሳደግ 17
አባሪዎች 17

# 1. መግቢያ

የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሀገራችን ያለችበትን የለውጥ ሂደት ውጤታማነት ለማረጋገጥ የተለያዩ የተቋማትና የሕግ ማሻሻያ ስራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ የነዚህ ማሻሻያ ስራዎች ዓላማ ለውጡ ተቋዋማዊ፣ ሁሉን አቀፍና በጥናት በተደገፈ አካሄድ ተግባራዊ ተደርጎ የሕግ በላይነትና ፍትህ የሠፈነባት፣ ሰብዓዊ መብቶች የተከበሩባት፣ በዲሞክራሲያዊ አግባብ የምትመራ ሀገር መገንባት ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከፍተኛ ልምድና ብቃት ያላቸውን አስራ ሶስት የሕግ ባለሞያዎች ያቀፈ "የሕግና ፍትህ ጉዳዮች አማሪ ጉባዔ" አቋቁሟል፡፡ አማካሪ ጉባዔዉ የሰብዓዊና ዴሞክራሲ መብቶችን እንዲሁም የሕግ የበላይነትን የመሳሰሉ ሕገ-መንግስታዊ መርሆዋች መሰረት በማድረግ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን በሕግና ፍትሕ ማሻሻያ ጉዳዮች ላይ የማማከር ስልጣን የተሰጠዉ ሲሆን የአማካሪ ጉባዔዉ ስልጣንና ተግባራት በዋናነት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

- በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ተቋማት ዉጤታማነት ላይ ተፅዕኖ ባላቸዉ ሕጎች፣ ተቋማትና አሰራሮች ላይ ጥልቅ የሆነ ጥናትና ግምገማ ማድረግ፤
- ተጠያቂነት የሰፈነበት የመንግስት አስተዳደር ለማስፈን፣ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥና ሕ-ገመንግስታዊ መብቶችን ሙሉ በሙሉ ለማረጋገጥ በሚደረገዉ ጥረት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን መለየት፣ ማጥናትና መሰብሰብ፤
- ሕጋዊና ተቋማዊ ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ አይነታዊ(ገላጭ) የጥናት ውጤቶች ላይ መሠረት ያደረጉ የማሻሻያ ሀሳቦችን የተጠኑና በፕሮግራም የተደገፉ እዉነታ ላይ የተመሰረቱ የማሻሻያ ፓኬጆችን ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቅረብ፡፡

አማካሪ ጉባዔዉ ስልጣንና ተግባሩን በሚገባ መወጣት ይችል ዘንድ የለት ከዕለት የአስተዳደር ስራ የሚያከናዉን የአማካሪ ጉባዔ ፅህፈት ቤት፣ በጎ ፈቃደኞችን እና ቋሚ ባለሙያዎችን ያካተተ የስራ ቡድኖች አቋቁሟል፡፡ የጉባዔዉ ጽ/ቤት አስተዳደራዊና የቴክኒክ ድጋፎችን ለስራ ቡድኖችና ለጉባዔዉ የሚሰጥ ሲሆን እያንዳንዱ የስራ ቡድን በተለያዩ ሕጎች ላይ ጥልቅ ጥናት በማድረግ የማሻሻያ ሀሳቦችን ያቀርባል፡፡ ይህ ዓመታዊ ሪፖርት በፕሮግራሙ አንደኛ ዓመት ዉስጥ በአማካሪ ጉባኤዉና በስሩ ባሉት የጉባኤዉ ጽ/ቤት እና የስራ ቡድኖች የተከናወኑ ስራዎችንና ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በማካተት እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

## 1.1 የለውጥ ሂደቱ ዳራ

አሁን በኢትዮጵያ እየተካሄደ የሚገኘዉ የሕግና ፍትሕ ማሻሻያ ፕሮግራም ከ20ኛዉ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ ሲካሄድ የቆየዉን የሕግና ፍትሕ ማሻሻያ ተከትሎ የመጣ ነዉ፡፡ በዚያ ዘመን ኢትዮጵያ ሕገ-መንግስታዊና ባህላዊ የሕግ ስርቷን ለማሻሻል ወደ ተለያዩ የዉጭ ሀገር የሕግ ሞዴሎች ማማተር ከመጀመሯም በተጨማሪ ዘመናዊነትንና የኢኮኖሚ ዕድገትን እዉን ለማድረግ በማሰብ ከፍተኛ የሆነ የሕግ ለዉጥ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ገብታለች፡፡ በኮሚኒስታዊ ርዕዮት ዓለም የታገዘው የደርግ መንግስት ወደ ስልጣን መምጣቱን ተከትሎ በኢትዮጵያ የነበረዉ የሕግና ፍትሕ ማሻሻል ሂደት ለጊዜዉ ተዳክሞ የቆየ

ቢሆንም ከደርግ መንግስት ዉድቀት በኋላ በተለይም ደግሞ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት መፅደቁን ተከትሎ ከፍተኛ የሕግ ማሻሻያዋች ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ ቀድሞ ሲደረጉ የነበሩት የሕግና ፍትሕ ሥርዓት የማሻሻል ጥረቶች በአጠቃላይ በቴክኒክ ረገድ ጥሩ የሚባሉ ቢሆኑም በየጊዜዉ በነበሩ አፋኝ የመንግስታት ፖሊሲዎች ምክንያት የታለመላቸዉን አላማ ሳያሳኩ ቀርተዋል፡፡ ይሁን እንጅ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ በሚያዝያ 2010ዓ.ም ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ መንግስታቸዉ በቀደመዉ ጊዜ ለተፈፀሙ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ የመብት ጥሰቶች ይቅርታ በመጠየቅ፣በሺዎች የሚቆጠሩ እስረኞችን በይቅርታና ምህረት በመልቀቅ፣ በመገናኛ ብዙሃንና በበይነመረብ ላይ የነበሩ ገደቦችን በማንሳት፣በሽብርተኝነት የተፈረጁ የፖለቲካ ድርጅቶችን ከሽብርተኝነት መዝገብ በማዉጣት እንዲሁም በስደት የነበሩ ጋዜጠኞች፣የማህበረሰብ አንቂዋችና የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ወደ ሀገራቸዉ እንዲገቡ በመፍቀድ አፋጣኝ የአጭር ጊዜ የመፍትሄ እርምጃችን ወስደዋል፡፡ መንግስት እንደ መካከለኛ ጊዜ ዕቅድ አፋኝና ለሰብዓዊ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ሕገ-መንግስታዊ መብቶች መከበር እንቅፋት የሆኑ እንደ ፀረ ሽብር፣የመገናኛ ብዙሃንእና የሲቪል ማህበረሰብ ሕጎችን ጨምሮ ለማሻሻል ቃል መግባቱ ይታወሳል፡፡

ለዴሞክራሲያዊነትና ሰብዓዊ መብቶች መከበር ትኩረት ከሰጠዉ አዲስ ፖለቲካዊ ነፃነት ጋር ተያይዞ አሁን እየተካሄደ የሚገኘዉ የሕግና ፍትሕ ሥርዓት ማሻሻል ሂደት ትኩረቱን በእነዚህ አዳዲስ የትኩረት አቅጣጫዋች ላይ አድርጓል፡፡ በተመሣሣይ መንግስት ይህ የሕግና ፍትሕ ማሻሻያ ሂደት የተለያዩ የሕግ ባለሞያዎችንና የሚመለከታቸዉን አካላት በማሳተፍ ነፃና ተቋማዊ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ወስኗል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የመንግስት የትኩረት አቅጣጫዎች እውን ለማድረግ በማሰብ የማሻሻያ ሂደቱን በነፃነት የሚመራ የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ ተቋቁሟል፡፡ አማካሪ ጉባዔዉ ከፖለቲካዊ ፍላጎት ይልቅ ነፃነትን፣ሙያን፣ስነ-ምግባርንና የአባላቱን አእዕምሮ መሠረት በማድረግ በማሻሻያ ሂደቱ ዉስጥ የመሪነት ሚና ይጫወታል፡፡ አማካሪ ጉባዔዉ የተቋቋመበትና የተዋቀረበት መንገድ በማሻሻያ ሂደቱ በኢትዮጵያና በዉጭ ሀገር የሚገኝን ልምድና እዉቀት በመጠቀም በስምንት የትኩረት አቅጣጫዋች ላይ መንግስትን ለማማከር ያለመ ነዉ፡፡

### 1.2 ዓላማ

የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ ዋና ዓላማ የኢትዮጵያ መንግስት ፍትሕን ለማሻሻል፣ የሕግ የበላይነትን ለማስከበር፣ ሰብዓዊ መብቶችን ለመጠበቅና እዉነተኛ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሀገር ለመገንባት የሚያደርገዉን ጥረት ዉጤታማ በሆነ መልኩ ማማከር ነዉ፡፡

# 2. የትግበራ አደረጃጀትና የሰዉ ሀይል

አካሪ ጉባዔዉ በመመሪያ ቁጥር 24/2010(አባሪ 2) መሠረት የተመሰረተ ሲሆን በኢትዮጵያ እየተካሄደ የሚገኘዉ የሕግና ፍትሕ ማሻሻል ሂደት አጠቃላይ አቅጣጫ ምን መሆን እንዳለበት መንግስትን የማማከር ኃላፊነት የተጣለበት ተቋም ነዉ፡፡ የአማካሪ ጉባዔዉ ዉሳኔዎችና የዉሳኔ ሀሳቦች አስገዳጅነት ባይኖራቸዉም እንኳን ጉባዔዉ የሚሰጣቸዉ የፖሊሲ አቅጣጫዎች

ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸውና በአጠቃላይ ተቀባይነት የሚያገኙ ናቸዉ፡፡ የአማካሪ ጉባኤዉና የጉባኤዉ ፅ/ቤት እንዲሁም ሌሎች በስሩ የተቋቋሙ ተቋማት አወቃቀር፣ ተግባር፣ ስልጣን እና ኃላፊነት በማቋቋሚያ መመሪያዉና(አባሪ 2) በአባሪ 3 በተቀመጡት ደንብና ሥርዓት መሠረት ተዘርዝሮ ይገኛል፡፡ አሁን እየሰሩ የሚገኙና የቀድሞ የጉባኤዉ አባላት አጭር የህይወት ታሪክ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ አንድ ተያይዟል፡፡

የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ ተቋማዊ አወቃቀር ከዚህ በታች በሚታየዉ ስዕላዊ መግለጫ ቀርቧል፡-




## 3. የ1ኛ ዓመት የስራ ዝርዝርና መርሀ-ግብር

የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔዉ በመጀመሪያው የስራ ዘመን የስራ ትግበራ መዋቅር መዘርጋት፣ መዋቅሩን በተወዳዳሪ ሰራተኞች ማደራጀት፣ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት፣ የስራ ቡድኖችን ማዋቀር፣ የጽ/ቤቱን እንዲሁም የጉባዔዉን ስራ የማስጀመር ተግባራት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ሰርቷል፡፡ በጉባዔዉ እና በጽ/ቤትና ተነሳሽነት የሚከተሉትን ተግባራት ተከናዉኗል፡-

- የስራ ቡድኖችንና የጽ/ቤቱን አባላት የመለመለ ሲሆን በቀጣይም እንዳስፈላጊነቱ ተመሳሳይ ስራ ያከናዉናል፣
- የጥናት ቡድኖችን የስራ አጀማመር ሪፖርት ተቀብሎ ገምግሟል፤፣
- ድረ-ገፅ፣ ኢሜል እና ድራይቭ አካዉንቶች ከፍቷል፣
- ለአማካሪ ጉባዔዉ የቀጥታ ድምፅ መስጫ ስዐርት ዘርግቷል፣,
  የስራ ቡድኖች የሥነ-ምግባር ደንብ በማዘጋጀት አፅድቋል፣
- አማካሪ ጉባዔው የሚመራበትን ውስጠ ደንብ አፅድቆ ተግባራዊ አድርጓል፣
- በተጨማሪም ጉባዔው የማሻሻያ ሥራውን የሚመራበት፣ አጠቃላይ ዓላማውንና የትኩረት አቅጣጫውን የሚያሳይ ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቶ አፅድቋል፣
- የህዝብ ተሳትፎ ስትራቴጂ ሰነድ ተዘጋጅቶ በስራ ላይ ውሏል፣
- የጉባዔዉ ጽ/ቤት የብዝሃነትና አካታችነት ፖሊሲ አዘጋጅቷል፣
- የጉባዔዉ ጽ/ቤት ሚስጥር ጠባቂነትና መረጃ ያለማዉጣት ፖሊሲ አዘጋጅቷል፣
- የገንዘብ ድጋፍና ወይም ሌሎች ትብብሮችን ዓለማቀፍ ተቋማት አግኝቷል፣

- አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በገንዘብ ድጋፍና በአጋር ድርጅቶች ትብብር በመታገዝ በየዘርፉ የሀገር ዉስጥና ዓለም አቀፍ ባለሙያዋችን ቀጥሯል፡፡

የስራ ቡድኖች  መቋቋማቸዉን ተከትሎ የአማካሪ ጉባዔዉ አቅም በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡፡ ይኸዉም 143(አንድ መቶ አርባ ሦስት) የረጅም ጊዜ በጎ ፈቃደኞች፣ 8(ስምንት) የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪዎች፣ 13(አስራ ሦሥት) የሀገር ዉስጥና የዉጭ የአጭር ጊዜ አማካሪዎች  በአማካሪ ጉባዔዉ ስር እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ተቋሙን በሰዉ ኃይል የማደራጀት ስራዉ እንደቀጠለ ሲሆን አማካሪ ጉባዔዉ በመጀመሪያ ዓመት የስራ ዘመኑ(በኢትዮጵያ አቆጣጠር 2011 ዓ/ም) ያለጉባዔዉ ተሳትፎ የማይታሰቡ ሕጋዊና ተቋማዊ ለዉጦችን ለማሳካት ተቃርቧል፡፡ በዕቅዱ መሠረት አማካሪ ጉባዔዉ ከሕግ ማውጣት ሂደት፣ ከፍትሕ ሥርዓት፣ ከወንጀል ፍትሕ ሥርዓት፣ ከፍትሐብሔርና አስተዳደር ሕግ ፍትሕ ሥርዓት እና ከዴሞክራሲያዊ ተቋማት ንዑስ መርሀ-ግብሮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ሕጎችን የማውጣትና ተቋማዊ ለውጥ ላይ ትኩረቱን አድርጎ ሰርቷል፡፡ በመጀመሪያዉ ዓመት መርሀ ግብር አማካሪ ጉባዔዉ ያከናወናቸዉ ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለዉ ይቀርባል፡፡

## 3.1 የፍትሕ ጉዳዮች የስራ ቡድን

በአማካሪ ጉባዔው የተቋቋመው የዳኝነት ጉዳዮች የጥናት ቡድን ስራውን የዳኝነት አካላት ነፃነትን በተመለከተ ጥያቄ በማያስነሳ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ይችል ዘንድ ከአዲሶቹ የጠቅላይ ፍርድ ቤት አመራሮች ጋር በተደረገ ምክክር በጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር መልሶ እንዲቋቋምና ስራውን እንዲሠራ ተደርጓል፡፡

## 3.2 የሲቪል ማህበረሰብ የስራ ቡድን

አማካሪ ጉባኤው ያቋቋመው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሕግ ማዕቀፍ የሥራ ቡድን በሥራ ላይ የነበረዉን "የበጐ አድራጐቶችና የማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001" ለማሻሻል የሚያስችል ፈጣን የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የሕግና ተቋማዊ የማማሻሻያ ምክረ-ሀሳቦችን እንዲያቀርብ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ የሲቪል ማህበረሰብ የስራ ቡድን አባላት ባብዛኛዉ ከሲቪል ማህበረሰብ ዘርፍ የተዉጣጡ ሲሆን የሕግ ባለሙያዋችን፣ሙሁራን፣የሲቪል ማህበረሰብ መሪዋች እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተቋማት የተካተቱበት ነዉ፡፡

የሲቪል ማህበረሰብ ሕግ ማሻሻያ መርሀግብር አማካሪ ጉባዔዉ ከዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ጋር ተያያዥ የሆኑ ኃላፊነቶቹን ለመወጣት ዓይነተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ተሰርቶበታል፡፡የስራ ቡድኑ የአዋጁን አተገባበርና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚዳስስ ጥናት አካሂዶ፤ በጥናቱ ግኝት መሠረት ባቀረበው ምክረ ሃሳብ አዲስ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሕግ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ሆኖ ፀድቋል ፡፡ በዚህ ሂደት የጥናት ቡድኑ በመላው ሃገሪቱ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያወያየ ሲሆን ሕጉ የመደራጀት መብትን የተመለከቱ ዓለም ዓቀፍና አህጉራዊ፣ እንዲሁም ሕገ-መንግስታዊ መርሆዎችን ባገናዘበ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

| የተከናወኑ ስራዋች | ቀን | ተግባሪ |
|---|---|---|

### ሂደት I – የዳሰሳ ጥናት/ሪፖርት

| | | |
|---|---|---|
| የስራ ቡድኑ የዳሰሳ ጥናት ጀመረ | ሰኔ 25.2010 | የስራ ቡድኑ |
| የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ለአማካሪ ጉባዔዉ ገቢ ሆነ | ነሀሴ22.2010 | የስራቡድኑ፣ፅ/ቤቱ |
| አማካሪ ጉባዔዉ ሪፖርቱን የገመገመበትና ቀጣይ ሂደቶችን አጸደቀ | ነሀሴ25.2010 | ጉባኤዉና ፅ/ቤቱ |

### ሂደት II – ሕግ ማርቀቅ

| | | |
|---|---|---|
| የሚመለከታቸዉ አካላት ዉይይት ከሲቪል ማህበረሰብ ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ጋር ተደርጓል። | ህዳር. 2011 | የስራ ቡድኑ፣ፅ/ቤቱ |
| በረቂቅ አዋጁ ላይ በዘጠኙ ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የህዝብ ዉይይት ተደርጓል። | ነሀሴ27-ጳጉሜ5.2010 | . የስራቡድኑ፣ፅ/ቤቱ |
| ረቂቅ የሲቪል ማህበራት አዋጅ ለአማካሪ ጉባዔዉ ገቢ ሆኖአል፡፡ | … | |
| አማካሪ ጉባኤዉ ረቂቅ አዋጁን ገምግሞ ትችቶችንና በየመፍተሄ ሃሳቦችን በመጨመር ገቢ አደረገ:: | ታህሳስ 2011 | አማካሪ ጉባዔዉ |

### ሂደት III – የሕግ ማዉጣት ሂደቱን መደገፍ

| | | |
|---|---|---|
| ረቂቅ ሕጉ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ለዉይይት ቀረበ:: | ጥር17. 2011 | የስራ ቡድኑ |
| አንግሊዘኛዉ ትርጓሜ ከአማርኛዉ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ ግምገማ ተደርጓል:: | መጋቢት6-9.2011 | የስራ ቡድኑና, የሲቪል ማህበራት ኤጀንሲ |
| የሲቪል ማህበራት አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ፀድቆ የሲቪል ማህበር ተቋማት ኤጀንሲ ተመሰረተ:: | መጋቢት3. 2011 | የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት |

### ሂደት IV – አፈፃፀም፣ድጋፍና ግምገማ

| | | |
|---|---|---|
| የኤጀንሲዉ የአፈፃፀም እቅድ ሰነድ የማዘጋጀት ሂደት ተጠናቋል.:: | መጋቢት 16. 2011 | የሲቪል ማህበራት ኤጀንሲና ፅ/ቤቱ |
| ደንቦችንንና መመሪያዋችን ለማርቀቅ የሚያግዝ የሀገር ዉስጥ ባለሙያ ለ30 ቀነ ተቀጥሯል:: | ሚያዝያ 7. 2011 | የሲቪል ማህበር ተቋማት ኤጀንሲ. |
| ደንቡን ለማርቀቅ ለኤጀንሲዉ ድጋፍ ተደርጓል:: | ከግንቦት1-23.2011 | ፅ/ቤቱ |
| በረቂቅ ደንቡ ላይ የምክክር ፎረም ተካሂዷል::. | ግንቦት 8.2011 | የሲቪል ማህበራት ኤጀንሲና ፅ/ቤቱ |
| ረቂቅ ደንቡ ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ገቢ ተደርጓል:: | ሰኔ13.2011 | የሲቪል ማህበራት ኤጀንሲና ፅ/ቤቱ |

## 3.3 የፀረ-ሽብር አዋጅ ማሻሻያ የስራ ቡድን

*የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ የፀረ ሽብር አዋጅ የስራ ቡድን ያደራጀ ሲሆን ይህ የስራ ቡድን በስራ ላይ ያለዉን የፀረ-ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 ይዘትና አተገባበር በማጥናት ሕጋዊና ተቋማዊ የማሻሻያ ሃሳቦችን በአጭር ጊዜ እንዲያቀርብ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ የስራ ቡድኑ አባላት የታወቁ የሽብር ወንጀል ተጠርጣሪዎች ተከላካይ ጠበቆችን፣ የዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ የዘርፉ ሙሁራንን እና የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሕግ ማርቀቅ ባለሙያዋችን ያካተተ ነዉ፡፡*

በስራ ላይ ያለዉ የፀረ -ሽብር አዋጅ በኢትዮጵያ ለተደረጉ የሰባዊ መብት ጥሰቶች መሰረታዊ ምክንያት ተደርጎ በመወሰዱ የዚህ አዋጅ ማሻሻያ መርሀ-ግብር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ የስራ ቡድኑ የፀረ- ሽብር አዋጁን እና አዋጁ በስራ ላይ የዋለበትን መንገድ የሚገመግም ጥናት አካሄዶ፣ በጥናቱ መስረት የመጨረሻ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቷል፡፡ ረቂቅ አዋጁ ቀድሞ ለሰባዊ መብት ጥሰት ምክንያት የነበረዉን ልዩ የምርመራ ሂደት በማስቀረት በመደበኛዉ የወንጀል ሕገ ምርመራ ሂደት እንዲሆን ከማድረጉም ባሻገር በሽብርተኝነት በመፈረጅ ሂደት ዉስጥ ሊደረጉ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዋቸን በጥልቀት አካቷል፡፡በጥናቱ ሂደት የሥራ ቡድኑ ተከታታይ የባለድርሻ አካላት የውይይት መድረኮችን አካሂዷል፡፡

| የተከናወኑ ስራዋች | ቀን | ተግባሪ |
|---|---|---|
| **ሂደት I – የዳሰሳ ጥናት/ሪፖርት** | | |
| የስራ ቡድኑ የዳሰሳ ጥናት ማድረግ ጀመረ | ሰኔ, 2010 | የስራ ቡድኑ |
| በዳሰሳ ጥናቱ ላይ ከዳኞች፣ ዐ/ህጎችና ጠበቆች ጋር የሚመለከታቸዉ አካላት ዉይይት ተደርጓል | …… | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤት |
| ከፖለቲካ ፓርቲዋችና የፖለቲካ አንቂዎች ጋር የህዝብ ዉይይት ተደርጓል | ……… | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤት |
| የዳሰሳ ጥናቱ ሪፖርት ለአማካሪ ጉባዔዉ ገቢ ሆኗል | ሀምሌ2010 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤት |
| **ሂደት II – ሕግ ማርቀቅ** | | |
| የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ መደበኛ ስብሰባ በፀረ-ሽብር ሕጉ ረቂቅ ላይ ዉይይት አካሂዷል | ኅዳር 28 2011 | |
| ከፖለቲካ ፓርቲዋች፣ ከመገናኛ ብዙሃን ተቋማት እና ሌሎች የመንግስት ተቋማት ጋር የአንድ ቀን ህዝባዊ ዉይይት በአዲስ አበባ ተካሂዷል። | የካቲት21 2011 | ፅ/ቤቱና የስራ ቡድኑ |
| ከሰብዓዊ መብት የሕግ ባለሙያዎች፣ ከሰብዓዊ መብት ተቋማት፣ ከቀይ መስቀል ማህበር እና በዉጭ ሀገር ከሚማሩ የሰብዓዊ መብት ተማሪዎች በረቂቁ ላይ ትችት ተቀብሏል | …. | ጽ/ቤቱ. |
| ረቂቅ የፀረ -ሽብር አዋጁን ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አስረክቧል | …. | ፅ/ቤቱና አማካሪ ጉባዔዉ |
| **ሂደትIII – የሕግ ማዉጣት ሂደቱን መደገፍ** | | |
| ረቂቅ ሽብርተኝነትመከላከልና መቆጣጠር አዋጁ ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉሟል | መጋ24 2011 | ፅ/ቤቱ |
| ረቂቁን በማጥራት ሂደት ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ድጋፍ አድርጓል | ሚያ 11, 2011 | የስራ ቡድኑ/ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ፅ.ቤቱ |
| ረቂቅ ሕጉን በማቅረብ ሂደት ላይ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ድጋፍ አድርጓል | ግን 11፣ 2011 | የስራ ቡድኑ/ጽ. ቤቱ |
| ረቂቅ ሕጉን ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በማቅረብ ሂደት ላይ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ድጋፍ አድርጓል | ሰኔ 11 2011 | የስራ ቡድኑ/ፅቤቱ |

## 3.4 የሚድያ ህግ የስራ ቡድን

የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ የመገናኛ ብዙሃን ሕግ የስራ ቡድን በነሀሴ 2011 ዓ/ም ያቋቋመ ሲሆን ይህ የስራ ቡድን በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ሕግ ላይ ሕጋዊና ተቋማዊ ጥናት በማድረግ የሚድያ ዘርፉ ዉስጥ ስር-ነቀል ሽግግር ሊያመጣ የሚያስችል ምክረ ሀሳብ እንዲያቀርብ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ የስራ ቡድኑ በዋናነት የየመገናኛ ብዙሃን፣ የመረጃ ነፃነት፣ የብሮድካስት፣የኮምፒተር ወንጀሎችና ሌሎች ሀሳብን በነፃ ከመግለፅ ጋር የተያያዙ ሕጎች ያለባቸዉን ክፍተት በመገምገም ምክረ ሀሳብ የማቅረብ ኃለፊነት ተጥሎበታል፡፡በጥናት ላይ የተመሠረተ ምክረ ሀሳብ ከማቅረብ ባሻገር ተደራሽና የጎለበተ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ የሚፈጥሩ የመገናኛ ብዙሃን ሕጎች እንዲያረቅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ይህ የስራ ቡድን ከሕግ ባለሙያዎች፣ጋዜጠኞች፣ የመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶች እና የፆታ ባለሙያዎች የተዉጣጡ አባላትን በማካተት የተቋቋመ ቡድን ነዉ፡፡

የመገናኛ ብዙሃን ሕግ የስራ ቡድን አማካሪ ጉባዔዉ በመጀመሪያ ካቋቋማቸዉ የስራ ቡድኖች መካከል አንዱ ቢሆንም የመገናኛ ብዙሃን ዘርፉ በሚያጋጥሙት ሕጋዊና ተግባራዊ ተግዳሮቶች እንዲሁም በጉዳዩ ስፋትና ጥልቀት ምክንያት የተጠበቀዉን ያህል መሄድ አልቻለም፡፡ሀሳብን በነፃነት የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት በኢትዮጵያ ከዓለም በጣም ዝቅተኛ ከሚባሉት ሀገራት መካከል ሲሆን እ.ኤ.አ በ2018 በተካሄደዉ የድንበር የለሽ ሪፖርተሮች ሪፖርት ከጠቅላላ 180 ሀገሮች 150ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች፡፡ይህን ተከትሎም የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ በአፍሪካ ደረጃም ቢሆን ዝቅተኛ ሲሆን ያሉት አብዛኞቹ ሚድያዎችም በመንግስት ቁጥጥር ስር ናቸዉ፡፡ ችግሩን ከስሩ ለመፍታት የስራ ቡድኑ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፉን ያቀጨጩ ሕጋዊ፣ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ርምጃዎች ለማጥናት ከፍተኛ ሰነዶችን መርምሯል፡፡ የስራ ቡድኑ የማሻሻያ ትኩረቱን እንዳስፈላጊነታቸዉ በቅደም ተከተል በመገናኛ ብዙሃን፣ በብሮድካስት፣ በመረጃ ነፃነት እና የኮምፒተር ወንጀል ሕጎች ላይ አድርጓ እየሰራ ይገኛል፡፡

| የተሰሩ ስራዎች | ቀን | ተግባሪ |
|---|---|---|
| **ሂደት I – የዳሰሳ ጥናት/ሪፖርት** | | |
| የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ለአማካሪ ጉባዔዉ ቀርቧል፡፡ | ጥቅምት 26-28.2011 | የስራቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| የመጀመሪያ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ለአማካሪ ጉባዔዉ ገቢ ሆኗል፡፡ | ኅዳ29.2011 | የስራቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| በረቂቅ የዳሰሳ ጥናቱ ላይ ሁለት የባለድርሻ አካላት ዉይይቶች ተካሂዷል፡፡ | የካቲት8.2011 | የስራቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በካፒታል ሆቴል 2ተኛ የባለድርሻ አካላት ዉይይት ተካሂዷል፡፡ | ኅዳር 29.2011 | የስራቡድኑና ፅ/ቤቱ |

ፓርቲዋች ምዝገባ ሕጎች ዙሪያ እየሰራ ይገኛል፡፡ ቅድሚያ ከተሰጣቸዉ ምርጫ ነክ ሕግ ማሻሻያዋች አኳያ የስራ ቡድኑ መቀመጫ ወደ የኢትዮጲያ ምርጫ ቦርድ የተዛወረ ቢሆንም የማሻሻያ ሂደቱ ከአማካሪ ጉባዔዉ ጋር የተቆራኘ ነዉ፡፡

| የተሰሩ ስራዋች | ቀን | ተግባሪ |
|---|---|---|
| **ሂደት I – የዳሰሳ ጥናት/ሪፖርት** | | |
| ይህ የስራ ቡድን በምርጫ ሕግ ቁጥር532/2000፣በፖለቲካ ፓርቲዎች የሥነምግባር ደንብና የፖለቲካ ፓርቲዋች ምዝገባ አዋጅ ላይ ጥናት በማድረግ ለአማካሪ ጉባዔዉ አስገብቷል | | የስራ ቡድኑ |
| ከሚመለከታቸዉ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አካላት ጋር በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና መ/ቤት ዉይይት አካሂዷል፡፡ | ጥቅምት6.2011 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| በዳሰሳ ጥናቱ ላይ ከፖለቲካ ፓርቲዋችና ሌሎች የሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በኢንተርኮንቲነንታል ሆቴል ዉይይት ተደርጓል፡፡ | ኅዳር13.2011 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| **ሂደት II ሕግ ማርቀቅ** | | |
| የሕግ ማርቀቅ ስራዉ ተጀምሯል፡፡ | | የስራ ቡድኑ |
| የኢትጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን መልሶ ለማደራጀት በወጣዉ ረቂቅ አዋጅ ላይ ከፖለቲካ ፓርቲዋችና ሌሎች አካላት ጋር በእሊሊ ሆቴል ዉይይት አካሂዷል፡፡ | ታኅሳስ 10.2011 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| በፖለቲካ ፓርቲዋች ምዝገባ አዋጅ፣ በፖለቲካ ፓርቲዋች የሥነ-ምግባር ደንብና በምርጫ ሥርዓት ላይ በቀረቡ የዳሰሳ ጥናቶች ዙርያ ከፖለቲካ ፓርቲዋችና ከማህበረሰብ አንቂዋች ጋር ዉይይት ተደርጓል፡፡ | ጥር1.2011 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| ከዓለም አቀፍ የምርጫ ባለሙያዋች ጋር በማሪዮት ሆቴል ዉይይት ተደርጓል፡፡ | | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| የሙሉ ሰዓት አማካሪ ተቀጥሯል፡፡ | … | |
| **ሂደት III – የሕግ ማዉጣት ሂደቱን መደገፍ** | | |
| የስራ ቡድኑ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን መልሶ ለማቋቋም የወጣዉን ረቂቅ አዋጅ ለህዝብ ተወካዮች እና ለሚኒስትሮች ም/ቤት በማቅረብ ሂደት ዉስጥ በም/ቤቶች ፊት በመቅረብ ረቂቅ አዋጁን ተከላክሏል፡፡ | | |

## 3.6 የሕግ አወጣጥ ሂደትና የአስተዳደር ሕግ የስራ ቡድን

የሕግ አወጣጥ ሂደትና የአስተዳደር ሕግ የስራ ቡድን የዓለም ባንክ “የቁጥጥር ፖሊሲና የአፈፃፀም ክለሳ(ቁፖአክ)” በሚል ርዕስ ባካሄደዉ ጥናት ባቀረበዉ ምክረ ሀሳብ መሰረት ነዉ፡፡የቁፖአክ ዓላማ የቁጥጥር ፖሊሲዋች፣ተቋማትና የአፈፃፀም ዘዴዋች በመለየትና በመከለስ የተሻሉ የአመራር ፖሊሲዎችን እዉን ማድረግ እንደሚቻል ማሳየት ነዉ፡፡አንደኛዉ የጥናቱ ግኝት በሕግ አወጣጥና ትግበራ ሂደት የሚታዩ ሕጎችን በንዑስ ሕጎች በየፈርጁ ከፋፍሎ በማዉጣትና በመፈፀም ሂደት ዉስጥ ያለዉን ክፍተት ማሳየት ነዉ፡፡በዚህም መሰረት ጥናቱ የተሸለ የአስተዳደራዊ ሕግ አወጣጥና አፈፃፀም ቅድመ ሁኔታዎችና ሥነ-ሥርዓቶች በተግባር ማዋል የሚያስችለዉን የአስተዳደር ሥርዓት ኮድ አስፈላጊነት በምክረ-ሀሳብነት አቅርቧል፡፡ በተጨማሪም የዚህ ንዑስመርሐግብር ዓላማ ሕጎቻችን ህዝብ አሳታፊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በይዘትም ይሁን በመሠረት ጥራታቸዉን የጠበቁ ሆነዉ እንዲወጡ ማድረግ ነዉ፡፡

በዚህም መሰረት የስራ ቡድኑ ያለዉን ረቂቅ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ በማጥናት ጥራቱን እንዲያሻሽል ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ በተጨማሪም የሕግ አወጣጥ ሂደቶችን በመገምገም የኢትዮጵያ ዋና ዋና ሕጎች ከሕገ-መንግስቱና ከዓለም-ዓቀፍ ስምምነቶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ የሚያስችል የሕግ አወጣጥ መንገዶችን የማምጣት ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ በተለያዩ አካላት የተዘጋጁ ረቂቅ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት ሕጎች መኖራቸዉን ተከትሎ የስራ ቡድኑ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በ2009 ዓ/ም ያዘጋጀዉን ረቂቅ የአስተዳደር አዋጅ አሻሽሎ እንዲያቀርብ ተወስኗል፡፡

| የተሰሩ ስራዎች | ቀን | ተግባሪ |
|---|---|---|
| **ሂደት I –የዳሰሳ ጥናት/ሪፖርት** | | |
| የስራ ቡድኑ የትግበራ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለአማካሪ ጉባኤዉ አስረክቧል፡፡ | ጥቅምት22.2011 | የስራ ቡድኑ |
| **ሂደት II –ህግ ማርቀቅ** | | |
| የነበረዉን የፌደራል የአስተዳደር ሕግ አዋጅ እንደገና አርቅቋል፡፡ | ከጥር-ሚያዝያ.2011 | የስራ ቡድኑ |
| በረቂቁ ላይ ዉይይት ተካሂዷል፡፡ | ከመጋቢት28-30.2011 | የስራ ቡድኑ |
| አማካሪ ጉባዔዉ በረቂቁ ላይ ተወያይቷል፡፡ | ሰኔ14.2011 | የስራ ቡድኑ |

## 3.7 የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት የስራ ቡድን

የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት የስራ ቡድንን አጠቃላይ የኢትዮጵያን የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት በማጥናት የማሻሻያ ምክረ ሀሳብ እንዲያቀርብ አቋቁሟል፡፡የስራ ቡድኑ 21 የዘርፉ ባለሙያዎችን በማካተት ነሃሴ 9 ቀን 2011 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን በተመሳሳይ ቀን ስራዉን ጀምሯል፡፡ የስራ ቡድኑ ከምስረታዉ ጀምሮ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ዙሪያ ጥቅል የመነሻ ጥናት ሲያዘጋጅ ቆይቷል፡፡የጥናት ቡድኑ በኢትዮጵያ የወንጀል የፍትሕ ሥርዓት ሁኔታ ላይ ጥናቱን ከታህሳስ መጀመሪያ እስከግንቦት መጨረሻ ድረስ እንዲጨርስ ይጠበቅ የነበረ ቢሆንም ከአማካሪ ጉባዔዉና ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጋር በመነጋገር በስራ ላይ ባለዉ የማረሚያ ቤት አዋጅ እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ አዋጅ ላይ ትኩረቱን አድርጎ እንዲሰራ ተወስኗል፡፡በዚህም መሰረት የተመረጡ የስራ ቡድኑ አባላት የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ያዘጋጀዉን ረቂቅ አዋጅ አሻሽሎ እንዲያቀርብ ተመድቧል፡፡በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የተዘጋጀዉ ረቂቅ አዋጅ በተፈፃሚነት ወሰንና የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ከማካተት አንፃር ሰፊ ለዉጥ ተደርጎበታል፡፡ የስራ ቡድኑ ረቂቅ አዋጁን ካሻሻለ በኋላ ከከፍተኛ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ዉይይት ተደርጎ የመጨረሻዉ ረቂቅ ምን መምሰል እንዳለበት መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

የወንጀል ሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕጉን በተመለከተ የስራ-ቡድኑ ረቂቅ የወንጀለኛ ሥነ-ሥርአት ሕጉን የካቲት 24 ቀን 2011 ዓ.ም ተቀብሎ በረቂቁ ላይ ዉይይት ተካሂዷል፡፡ ረቂቅ የወንጀል ሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ አዋጁ በፍጥነት እንዲጠናቀቅ መወሰኑን ተከትሎ የስራ ቡድኑ ሌሎች ኃላፊነቶችን በመተዉ በዚህ ረቂቅ ላይ ሙሉ ጊዜዉን ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡

| የተሰሩ ስራዎች | ቀን | ተግባሪ |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| **ሂደትI – የዳሰሳ ጥናት/ሪፖርት** | | |
| የስራ ቡድኑ በአግባቡ ተቋቁሞ ይፋ ሆኗል፡፡ | ነሀሴ11.2011 | |
| የሙሉ ጊዜ አማካሪ ተቀጥሯል፡፡ | | |
| የመነሻ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለአማካሪ ጉባዔዉ ገቢ ሆኗል፡፡ | ጥቅምት23.2011 | የስራ ቡድኑ |
| የስራ ቡድኑ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት አስረክቧል፡፡ | | የስራ ቡድኑ |
| ያለዉን ረቂቅ ለማሻሻል ዉሳኔ ተላልፏል፡፡ | | አማካሪ ጉባዔዉ |
| **ሂደት II –ሕግ ማርቀቅ** | | |
| በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ ስራ ተጀምሯል፡፡ | መጋቢት7.2011 | |
| የስራ ቡድኑ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ረቂቅ አዋጆች ለአማካሪ ጉባዔዉና ለፅ/ቤቱ አስረክቧል፡፡ | ______________ | የስራ ቡድኑ |
| አማካሪ ጉባዔዉ ረቂቅ የፌዴራል ማረምያ ቤቶች አዋጁን ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አስረክቧል፡፡ | | |
| ረቂቅ የፌዴራል ማረምያ ቤቶች አዋጁ ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉሟል፡፡ | መጋቢት9.2011 | የስራ ቡድኑና አማካሪ ጉባዔዉ ፅ/ቤቱ |
| የስራ ቡድኑ ረቂቅ የወንጀለኛ ሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ አዋጁን ለአማካሪ ጉባዔዉ አስረክቧል፡፡ | መጋቢት23.2011 | የስራ ቡድኑና አማካሪ ጉባዔዉ ፅ/ቤቱ |
| በረቂቅ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ አማካሪ ጉባዔዉና የስራ ቡድኑ የጋራ ምክክር አካሂደዋል፡፡ | ሚያዝያ2.2011 | |
| የመጨረሻዉ አማርኛ ረቂቅ የወንጀለኛ ሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ አዋጅ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ገቢ ሆኗል፡፡ | ሚያዝያ4-6.2011 | የስራ ቡድኑ፣ አማካሪ ጉባዔዉ ፅ/ቤቱ |
| የመጨረሻዉ እንግሊዝኛ ረቂቅ የወንጀለኛ ሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ አዋጅ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ገቢ ሆኗል፡፡ | ሰኔ15.2011 | የስራ ቡድኑ |
| | _________ | የስራ ቡድኑና አማካሪ ጉባዔዉ |

## 3.8 የንግድና የፍትሐብሔር ሕግ የስራ ቡድን

የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ በኢትዮጵያ የንግድ እንዲሁም የፍትሐብሔር ሕግ ዙርያ ያሉ ማነቆዎችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ እንዲያቀርብ በነሀሴ 2010 ዓ.ም የንግድና ፍትሐብሔር ሕግ የስራ ቡድን ያቋቋመ ሲሆን የስራ ቡድኑ አስር የትርፍ ሰዓት በጎ ፈቃደኛ አባላት ብቻ ነው ያሉት፡፡ ለረጅም ጊዜ በሥራ ላይ የቆየውን የንግድ ሕግ ለማሻሻል ከዚህ ቀደም የተጀመረው ሥራ በቅርቡ ተጠናቆ ረቂቅ የንግድ ሕጉ የተዘጋጀ ቢሆንም ይህን ዓይነት ሕግ ለሃገሪቱ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ፣ በኮድ_መልክ የሚዘጋጁ ሕጎች ሊኖራቸው የሚገባውን ዘመን ተሻጋሪ ባህሪና የንግድ እንቅስቃሴ በአሁኑ ወቅት ከመቼውም ጊዜ በላይ ድንበር ተሻጋሪ እየሆነ መምጣቱን ከግምት ባስገባ መልኩ ረቂቁን መከለስና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለዚህ ሥራ በአማካሪ ጉባዔው የተቋቋመው የስራ ቡድን ረቂቅ የንግድ ሕግ ኮዱን በዝርዝር እየገመገመ ሲሆን፣ ከዓለም ዓቀፍ ባለሞያዎች ጋር በመተባበር የክለሣ ሥራውን በማካሄድ ላይ ነው፡፡

| የተሰሩ ስራዋች | ቀን | ተግባሪ |
|---|---|---|
| **ሂደትI – የዳሰሳ ጥናት/ሪፖርት** | | |
| በአምስቱም የንግድ  መፅሀፎች ላይ የዳሰሳ ጥናት ተደርጎ ለሁሉም የስራ ቡድኖች ተሰጥቷል | የካቲት 1.2011 | በተለያዩ የኮዱ መፅሀፍት ላይ የሚሰሩ ንዑስ የስራ ቡድኖች |
| በዳሰሳ ጥናቱ ላይ ዉይይት የተደረገ ሲሆን የስራ ቡድኑ የረቂቅ የንግድ ሕጉ መፅሀፍ 3 እና 4 ማለትም ስለ ጭነትትና ኢንሹራንስ ጉዳዩች ብዙ የጎደሉ ነገሮች እንዳሉ ገልጾል፡፡በተጨማሪም የኪሳራ ሕጉንና | የካቲት4.2011 | የስራ ቡድኑ |

| | | |
|---|---|---|
| የኤሌክትሮኒክ ክፍያን በተመለከተ የዉጭ ባለሙያ እንደሚያስፈልግ አስምሮበታል፡፡ | | |
| የስራ ቡድኑ ድርጅቶችን የተመለከቱ(መፅሀፍ 1፣2፣5) ጉዳዮች ብቻዉን ሕግ ሆኖ እንዲወጣ ለአማካሪ ጉባዔዉ ምክረ ሀሳብ አቅርቧል፡፡የኢንሹራንስ፣ ባንክና መጓጓዛን የተመለከተዉ (መፅሀፍ 3 እና4) ሕግ ብቻዉን ሕግ ሆኖ እንዲወጣ ምክረ ሀሳብ አቅርቧል፡፡ | የካቲት23.2011 | የስራ ቡድኑ |
| የንግድ ሕጉ መፅሀፍት1፣2 እና 3 ብቻዉን ሕግ ሆኖ እንዲወጣ ምክረ ሀሳብ ያቀረበዉ ሪፖርት ለአማካሪ ጉባዔዉ ገቢ ሆኗል፡፡ | መጋቢት7.2011 | የስራ ቡድኑ |
| አማካሪ ጉባዔዉ መፅሀፍት1፣2 እና 3 ብቻዉን ሕግ ሆኖ እንዲወጣ የቀረበዉን ምክረ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡ | መጋቢት.2011 | የስራ ቡድኑ |
| **ሂደት II –ሕግ ማርቀቅ** | | |
| የንግድ ሕጉ ድርጅት ተኮር መፅሀፍት(መፅሀፍ1፣2 እና 5) የማርቀቅ ሂደቱ እንደቀጠለ ሲሆን 3ኛ እና 4ተኛ መፅሀፍት ቆይተዉ የሚወጡ ይሆናል፡፡ | | |
| ለኪሳራና ሕግ ማሻሻያ የሀገር ዉስጥም ይሁን የዉጭ የባለሙያ ድጋፍ የመለየትና የማግኘት ሂደቱ በቂ አለመሆኑ ታዉቋል፡፡<br>1. ፕሮፌሰር ሪቻርድ ዳማን ከፈረንሳይ ሶርቦን ዩኒቨርሲቲ፣<br>2. የኮመን ሎዉ የኪሳራ ሕግ ባለሙያ የሆኑት ሚስ አንቶኒያ ፐርኮሳ ኢትዮጵያዊ ባለሙያዋችን ለመደገፍ የተስማሙ ሲሁን በኤሌክትሮኒክ ግንኙነቶች ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡<br>3. ሁለቱ ባለሙያዎች የማርቀቅ ሂደቱን ለማጠናቀቅ ለሁለት ቀናት ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጡ ይጠበቃል፡፡ | መጋቢት.2011<br>ከግንቦት7-ግንቦት12.2011 | |
| መፅሀፍ 1 እን 2 የማርቀቅ ሂደት ተጠናቋል | | |
| የመፅሀፍ አምስትን የማርቀቅ ሂደት ለማጠናቅ 3 ኢትዮጵያዊያንና እና 4 የዉጭ ባለሙያዋች ተገኝተዋል፡፡ | ሰኔ 27-ሀምሌ1.2011 | |

## 3.9 የህሕግና ተያያዥ ጉዳዮች አገልግሎት የስራ ቡድን

የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ የሕግ ሙያ ዘርፉ ለሰፊዉ ማህበረሰብ እየሰጠ ያለዉን አገልግሎት የሚያጠናና የማሻሻያ ምክረ ሀሳብ የሚያቀርብ የሕግና ተያያዥ ጉዳዮች አገልግሎት የስራ ቡድን አቋቁሟል፡፡ የስራ ቡድኑ ከሕግ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተገናኘ ያሉ ሕጋዊና አስተዳደራዊ ዉስንነቶች በተለይም ከተደራሽነትና ከአገልግሎት ሰጭዎች የሙያ ሥነ -ምግባር ጋር የተገናኙ ችግሮችን በመለየት ሊወሰዱ የሚገቡ ርምጃዋችን እንዲያቀርብ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ በተጨማሪም ፍትህንና የማህበሩን ጥቅም ከግምት ዉስጥ በማስገባት የህግ አገልግሎት አቅራቢዎች አማራጭ የቁጥጥር ሥርዓት እንዲያቀርብም ይጠበቃል፡፡ የሕግ ሙያ ለሕግ የበላይነት ያለዉን አይነተኛ ሚና እና በዘርፉ ላይ ሲደርሱ ከነበሩ ተፅዕኖዋች አንፃር የስራ ቡድኑ የሕግ ስራን ከአስፈጻሚዉ ነፃ ሆኖ ለመስራት የሚያስችል የሕግ ስራ አዋጅ ማርቀቅ ላይ ሙሉ ትኩረቱን አድርጎ እየሰራ ይገኛል፡፡

| የተሰሩ ስራዋች | ቀን | ተግባሪ |
|---|---|---|
| **ሂደትI – የዳሰሳ ጥናት/ሪፖርት** | | |
| ረቂቅ የዳሰሳ ጥናት ተዘጋጅቷል | ጥቅምት 28.2011 | የስራ ቡድኑ |

| | | |
|---|---|---|
| ዓለም አቀፍ ባለሙያዎችና የስራ ቡድኑ በዳሰሳ ጥናቱ ላይ የመነሻ አስተያየታቸዉን አስገብተዋል | ታህሳስ 1.2011 | የስራ ቡድኑ |
| የመጨረሻዉን የዳሰሳ ጥናት ለአማካሪ ጉባዔዉ አስገብቷል | ጥር7.2011 | የስራ ቡድኑ |
| የስራ ቡድኑ ጥናቱን ለአማካሪ ጉባዔዉ አቅርቧል | … | የስራ ቡድኑ |
| አማካሪ ጉባዔዉ ጥናቱን በማፅደቅ ምክረ ሀሳቡን ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አስገብቶ የስራ ቡድኑ የሕግ ማርቀቅ ሂደቱን እንዲቀጥል ወስኗል፡፡ | … | አማካሪ ጉባዔዉና ፅ/ቤቱ |

**ሂደት II –ሕግ ማርቀቅ**

| | | |
|---|---|---|
| የስራ ቡድኑ ያሉ አማራጮችን በተመለተ ከአማካሪ ጉባዔዉ የማብራሪያ መልሶችን በመቀበል የማርቀቅ ስራዉን ጀምሯል፡፡ | የካቲት4.2011 | የስራ ቡድኑ |
| በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ የሕግ ማህበረሰብ አካላትና እንዲሁም ከፍትሕና የመንግስት አካላት ጋር በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አዳራሽ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ተካሂዷል፡፡ | መጋቢት25.2011 | የስራ ቡድኑና አማካሪ ጉባዔዉ |
| ከሕጉ ማህበረሰብ፣ ከፍትሕና መንግስት የሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በባህር ዳር ህዝባዊ ዉይይት ተደርጓል፡፡ | መጋቢት26.2011 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| ከሕጉ ማህበረሰብ፣ ከፍትሕና ከመንግስት የሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በሐዋሳ ህዝባዊ ዉይይት ተደርጓል፡፡ | መጋቢት27.2011 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| ረቂቅ ሕጉና የማብራሪ ጽሁፎች ለአማካሪ ጉባዔዉ ገቢ ሆነዋል፡፡ | ሚያዝያ14.2011 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| በጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት፣ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና የህግ ባለሙያዎች ማህበር በመሩት ስብሰባ ከፍተኛ ቁጥር ካላቸዉ ጠበቆች ጋር በአዲስ አባባ ህዝባዊ ዉይይት ተደርጓል፡፡ | ሚያዝያ23.2011 | የስራ ቡድኑ፣ጠ/ዓ/ህግና ፅ/ቤቱ. |
| አማካሪ ጉባዔዉ በረቂቁ ላይ ተወያይቶ ለስራ ቡድኑ አቅጣጫ አስቀምጧል | ሚያዝያ25.2011 | አማካሪ ጉባዔዉየስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| የጠበቆች አዋጅ ዜሮ ረቂቅ ተጠናቋል | ግንቦት13.2011 | የስራ ቡድኑ |
| የጠበቆች ረቂቅ አዋጅ ወደ አማርኛ ተተርጉሟል | ግንቦት28.2011 | ፅ/ቤቱ |
| ከአዲስ አበባና ከክልል ከተዉጣጡ የሕግ ባለሙያዎች ጋር በአዲስ አበባ ዉይይት ተደርጓል | ሰኔ8.2011 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ |
| ከክልል የፍትህ ቢሮዎችና የሕግ ባለሙያ ማህበራት ጋር ዉይይት ተደርጓል | ሰኔ9.2011 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ. |
| የመጨረሻዉ ረቂቅ አዋጅ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ገቢ ሆኗል | ሰኔ28.2011 | የስራ ቡድኑና ፅ/ቤቱ. |

# 4. ተግዳሮቶች እና የቀጣይ ጊዜ ተስፋዎች

በ3ኛው ክፍል ለመግለጽ እንደተሞከረው አማካሪ ጉባዔው በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ስራዎችን ማከናወን ችሏል፡፡ ከተረቀቁት ሕጎች ውስጥ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ በየመስካቸው የበኩላቸውን በጎ ተጽዕኖ መፈጠር ጀምረዋል፡፡ ሁለት ኮዶችን ጨምሮ 12 የሚደርሱ ሕጎች ለፓርላማው እንዲቀርቡ ለማድረግ እየተሰራ ነው፡፡ ይህ ቢሰራም እንኳን አማካሪ ጉባዔው የገጠሙት ወይም ወደፊት የሚገጠሙት ፈተናዎች አይኖሩም ማለት አይደለም፡፡ ከታች የተዘረዘሩት የፈተናዎቹ ማሳያዎች ናቸው፡፡

### 4.1. የሰው ሀብት

በአማካሪ ጉባዔው ስር እየተካሄደ ባለው የሕግ እና የፍትሕ ማሻሻያ ስራ ውስጥ ትልቁ ጥንካሬ በሕግ፣ በሲቪል ማህበረሰብ፣ በመገናኛ ብዙሃን፣ በሰብዓዊ መብት እና በዲሞክራሲ ደጋፊ የማህበረሰቡ አካላት የስራ ጫናውን በማቃለል እና ማሻሻያውን በመምራት ረገድ የታየው ቁርጠኝነት የሞላበት ድጋፍ ነው፡፡ እነዚህ የተለያዩ አካላት ይህ አጋጣሚ መታለፍ የሌለበት ታሪካዊ ዕድል እንደሆነ በማመን ለቀረባለቸው ጥሪ የሰጡት ምላሽ ሲታይ በማሻሻያው ስራ ላይ በበጎ ፈቃደኝነት ያሳዩት ንቁ ተሳትፎ የሚያስገርም አይሆንም፡፡

የላቀ ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች በተጣበበ ጊዜ ውስጥ በበጎ ፈቃድ እንዲሰሩ በማድረግ ማስተባበር እና በቁጥጥር ረገድ እንዲሁም የበጎ-ፈቃደኞች መሰላቸት እና ግራ-መጋባት ጋር በተያያዘ ተግዳሮት ሊኖር እንደሚችል ከጅምሩ ይገመት ነበር፡፡ የአማካሪ ጉባዔው ፅ/ቤት በቂ የሰው ኃይል አለመኖሩ እና ፅ/ቤቱ ራሱ በጎፈቃደኛ ሰራተኞች ያሉበት መሆኑ በጎፈቃደኞችን በማስተዳደር በኩል ድክመት እንዲኖርበት ሆኗል፡፡ ተሳታፊዎቹ በማሻሻያው ሂደት ያበረከቱት እና ያሳዩት ቁርጠኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ የአማካሪ ጉባዔው ስራ በበጎ ፈቃድ ላይ መመረኮዙ በዕቅድ፣ ቁጥጥር እና ውጤታማነት ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ሲሆን ከጊዜ ሰሌዳ እና ከልዩ ልዩ የፋይናንስ/ቢዝነስ አስተዳደር እቅዶች ጋር አብሮ ለመሄድ ተቸግሯል፡፡

ጉባኤው በ2ኛ ዓመቱም ስራውን ሲሰራ የበጎ-ፈቃድ ስራን፣ የሙሉ ጊዜ ሰራተኞችን እና አማካሪዎችን ተግባር አቻችሎ በመሄድ ይሆናል፡፡

### 4.2. ቢሮና መሳሪያዎች

አማካሪ ጉባዔው ከጅምሩ ጀምሮ የገጠመው ሌላው ተግዳሮት ስራውን ለመከወን የሚያስፈልጉ የመሳሪያዎች አቅረቦት ችግር ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው ፈተና የቢሮ አቅርቦት ነው፡፡ ምንም እንኳን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ለአማካሪ ጉባዔው የቢሮ አቅርቦት ቢያደርግለትም ሁሉንም ተግባሮች ለመፈጸም ቢሮው በቂ አልነበረም፡፡ በመሆኑም የአማካሪ ጉባዔው፣ የጽ/ቤቱ እና የስራ ቡድኖች ስብሰባዎች የሚካሄዱት በተውሶ በተገኙ ቢሮዎች ነው፡፡ አማካሪ ጉባዔው በሳምንት 2 ጊዜ ለሚያካሂደው መደበኛ ስብሰባ እና አስቸኳይ ስበስባዎች ሲያካሂድ እንኳን በተውሶ የተገኙት ቢሮዎች በሌሎች ስብሰባዎች መያዛቸውን ሲያውቅ የስብሰባ ቦታ ለመቀየር ይገደዳል፡፡ አማካሪ ጉባዔው በአሁኑ ሰዓት የቢሮ ችግርን ለመፍታት የገንዘብ ድጋፍ (ፈንድ) በማፈላለግ ላይ ይገኛል፡፡

ከቢሮ ችግር ባሻገር በአሁኑ ሰዓት አማካሪ ጉባዔው ተግባሩን በአግባቡ ለማከናወን የሚረዱት መሳሪያዎች የሉትም፡፡ የኮምፒዩተር፣ የኢንተርኔት፣ የተንቀሳቃሽ ስልክ፣ የመጓጓዣ ወጪዎች እና የህትመት ወረቀቶች ወጪዎች የሚሸፈኑት በሰራተኞች እና በበጎ-ፈቃደኞች ነው፡፡ ይህ የአማካሪ ጉባዔው ሰራተኞች እና በጎ-ፈቃደኞች ተግባር የሚደነቅ ቢሆንም አማካሪ ጉባዔው ለሰራተኞቹ እና በጎፈቃደኞቹ ከስራ መሳሪያዎች በተጨማሪ ንፁኅና ምቹ የስራ ቦታ ከመፈጠር ግዴታው ነፃ አያደርገውም፡፡

### 4.3. በማሻሻያ ሂደቱ የሚደረግ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ

የበጀት እጥረቱ እንዳለ ቢሆንም አማካሪ ጉባዔው ህዝባዊ ውይይቶችን በማከናወን ረገድ የተሻለ ስራ ሰርቷል፡፡ የዲሞክራሲ ችግሮችን ለመፍታት ሰፊ የሆነ የዜጎች ተሳትፎ ስለሚያስፈልግ፣ ከአጋሮች በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እና በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

እንዲሁም ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተደረገ አስተዳደራዊ ድጋፍ አማካሪ ጉባዔው በርካታ ህዝባዊ ውይይቶችን በተለይም በአዲስ አበባ ማካሄድ ችሏል፡፡ በርካታዎቹ ህዝባዊ ውይይቶችም የሚዲያ ሽፋን ማግኘት ችለዋል፡፡ በዚህ ረገድ የተሻለ ስኬት ማስመዝገብ ቢቻልም ከአዲስ አበባ ውጪ ውይይቶችን ማካሔድ እና የተሻለ የሚዲያ ስትራቴጂ መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡

### 4.4. ማህበረሰብ አቀፍ ንቃት ማሳደግ

ከላይ እንደተገለፀዉ የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ ካለበት ከፍተኛ የሰዉ ሀይል እጥረት አንፃር ጉባዔዉ በአንፃራዊነት መልካም የሚባል የህዝብ ዉይይቶች አካሂዷል፡፡ነገር ግን የዉይይት ዉጤቶችንና ሌሎች ስራዋችን ከሚድያ ፍጆታ ባለፈ ዘላቂነትና ተደራሽነት ባለዉ ፕላትፎርም ማሳተም አልተቻለም፡፡ ቋሚ የህዝብ ግንኙነት አማካሪ ለመቅጠር የሚያስችል ገንዘብ በማፈላለግ ላይ ሲሆን ለጊዜዉ ስራዋቹን በሚገባ ለማስተዋወቅ የሚስሉ ድህረ-ገፆችና ማህባራዊ ሚድያ አማራጮችን ለመጠቀም አስቧል፡፡ ይሁን እንጅ የታሰቡትን መገናኛ መንገዶች በሰዉ ኃይል እጥረት ምክንያት ሙሉ በሙሉ መጠቀም አልተቻለም፡፡

### 4.5. የማሻሻያዉ ዉጤታማነት እና ቀጣይነት

የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ ወደ ሁለተኛ ዓመቱ እየተሸጋገረ ባለበት ወቅት አሁንም እየገጠመዉ ያለዉና በቀጣይም ሊገጥመዉ የሚችልዉ ዋና ፈተና የተደረጉ ማሻሻያዎች ስኬትና ድክመት የግምገማ ስርዐት ማስቀመጥና በዘላቂነት ድጋፍ የማድረግ ጉዳይ ነዉ፡፡ አብዛኛዋቹ የሚካሄዱት ማሻሻያዋች በተቋማትና አንዳንዴም በግለሰቦች ስልጣን ላይ ገደብ የሚያደርጉ በመሆናቸዉ ከእነዚህ አካላት ሊመጣ የሚችለዉን ተቃዉሞ ሊፈታ የሚችል ስትራቴጅ መዘርጋትና ማሻሻያዉን በህዝብ ተሳትፎ ህዝባዊ መሰረት ያለዉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

# አባሪዎች

አባሪ 1 አሁን በማገልገል ላይ ያሉና የቀድሞ የአማካሪ ጉባዔዉ አባላት አጭር የህይወት ታሪክ

(ያልተሟላ)

አባሪ 2 የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ(አዋጅ ቁጥር 24/2010)

አባሪ 3 የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ የሥነ ስርዓት ደንብ